ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ከግንቦት ፲ እስከ ፲፪ ፪ሺ፫ ዓም ከሐዋርያት ተያይዞ የመጣው የርክበ ካህናት ዓመታዊ መደበኛ ጉባኤ በካልጋሪ ካናዳ ደበረ ምህርት ቅዱስ ገብረኤል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አካሀዶዋል። ጉባኤው ታሪካዊት ሐዋርያዊት ብሔራዊት በሆነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በምታካህዳቸው መንፈሳዊና መህበራዊ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት አድርጓል

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ይህን ለሠላሳ አንደኛ ጊዜ የምታካሂደውን ጉባኤ በስደት ላይ ሁና ስታደርግ በአንድ በኩል ቀኖናን ጠብቃ ለማስጠበቅ ይህን ታሪካዊ ግዴታ ከሚደግፏት ምእመናን ጋር በመሆን እየተወጣች መሆኗ ሲያስደስታት በሌላ በኩል ደግሞ አሁን ቤተክረስቲያኒቱና አገሪቱ ያለችበትን ሁኔታ ስታይ ሐዘን ይሰማታል። በመሆኑም ይህ ጉባኤ ሌሎች ጉባኤዎች ከሚሉት የተለየ የቤተክርስትያንን ችግር የተመለከተ ጉባኤ ነው።

ስለቤተክርስቲያ አንድነት ይህ ጉባኤ ከሁሉም በላይ በጥልቅ የተመለከተው በሁሉም ምዕመናን ዘንድ መወያያ የሆነው ቀኖና ተጥሶ ሕገወጥ ፓትርየርክ በመሾሙ ምክንያት ቤተ ክርስቲያኒቱ በአሁኑ ጊዜ በስደት ላይ እንድትከራተት ያደረጋትና ከሁለት የከፈላት ጉዳይ ነበር። ሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ይህ ልዩነት ተወግዶ ቀኖና ቤተክርስቲያን ተጠብቆ ቤተክርስቲያን በሰላም እንድትኖር በጽኑ ያምናል። ለዚህም በትጋት ይሠራል። ይህን አስመልክቶ በአሁኑ ጊዜ በዚሁ ዙሪያ ስለሰላምና አንድነት እያደረገ ያለውን እንቅስቃሴ የሰላምና አንድነት ጉባኤ ስለቤተክርስቲያን ሰላም በጀመረው መሠረት ያቀረበውን ሪፖርትና ጥያቄ እንዲሁም ከአዲስ አበባ በኩል የቀረበውን በሰላም ስም ያወጡትን የውሳኔ ሠነድ አስመልክቶ የሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ የሰላም ኮሚቴ የሰጠውን መልስ በንባብ አድምጦ በአሁኑ ወቅት በቤተክርስቲያን ስም የሚንቀሳቀሱ ቡድኖች የሚነዙትን ውዥንብር፤ በአገር ውስጥ የሚኖረው ሕዝብ ያለበትን መከራና ችግር፤ እንዲሁም በውጭ አገር ያሉት አብያተክርስቲያናት የሚጠናከሩበትን ሁኔታ በመመርመርና በማጥናት ቤተክርስቲያን የወደፊት አቅጣጫና እድገት ስለ አገልጋይ ካህናት የሙያ ማሻሻያ ኮርስ ስለህጻናትና ወጣቶች ሰንበት ትምህርት ቤት መጠናከር በሚሉት አጀንዳዎች በሰፊው ከተወያ በኋላ ለቤተ ክርስቲያን እድገት ጠቃሚ መመሪያዎች ውሳኔዎችን አጽድቆ የሚከተለውን የአቅዋም መግለጫ አውጥቷል።

1. ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ ያጋጠማትን ችግር ለመፍታት ቀኖና ተጠብቆ ሰላምና አንድነት እንዲመሠረት ጥረት በማድረግ ላይ ያለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤ የጻፈው ደብዳቤ በስደት ላለው ሲኖዶስ ደርሶት በሰፊው ተወያይቶበታል።እንዲሁም በጥልቀት በአባሪ ተያይዞ ከአዲስ አበባ የተላከ የስብሰባ ቃለ ጉባኤና ውሳኔ ደርሶት ጉባኤው ተመልክቶታል።

ለሰላምና ለአንድነት የሚቀርብ ጥያቄ እንኳን ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታይ ይቅርና ለማንኛውም ለሰው ልጅ ሁሉ ተቀባይነትና አግባብነት ያለው ነው። የሰላምና የአንድነት አለመኖር ቤተ ክርስቲያንን ከመጉዳት በስተቀር ሌላ የሚሰጠው ጥቅም የለም። በመሆኑም ይህ ሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ የሰላምና የአንድነቱን ድርድር ንደፈ ሐሳብ በሙሉ ልብ የተቀበለው ቢሆንም ከአዲስ አበባ የተላከው የሰነዱ አባሪ ውስጠ ይዘት ግን፡-

ሀ. የእርቅ ፍሊጋ፤ የሰላና የአንድነት መደራደሪያ ነጥብ ያዘለ ሳይሆን በአንድ ወገን ብቻ በቅድሚያ የተደረገ ውሳኔን እንዲታወቅላቸው የተላከ መረጃ ስለሆነ፤

ለ. የአባሪው ሰነድ ይዘት ስለ ሰላም አስፈላጊነት ይተንትን እንጇ በአብዛኛው ከእውነት የራቀና የጉዳዩን ሥረ መሠረት የሳተና የዋሁን አንባቢ ሕዝበ ክርስቲያን የሚያሳሳት የተቀነባበረ ሰነድ በመሆኑ፤

ሐ. የሕዝበ ክርስቲያኑ ሠላምና አንድነት የሚሰፍነው የተጣሰው ህገ ቤተ ክርስቲያንና የፈረሰው ቀኖና ሲጠበቅ ብቻ መሆኑ እየታወቀ፤ የአባቶችን መሰደድና አገር ሊናፍቁ የሚችሉ መሆኑን መሠረት በማድረግ የሚለገስ ችሮታ አድርገው ማቅረባቸው አሳፋሪ ድርጊት ስለሆነ፤

ቅዱስ ሲኖዶሱ አይቀበለውም።

ብሎም እያንዳንዱን የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ አባል፤ አባቶችና ምእመናንን ጨምሮ ተንከባክባ ካሳደገች እናት ሐገር ርቆ ለስደት የዳረገን የፍትህ መጓደል ዋናኛ መንስኤነትን ለማቃለልና እውነታው ከሕዝብ እይታ እንዲሠወርና አቅጣጫውን ለማሳት የተደረገ ሙከራ ነው።

*ስለዚህ ይህ ሕጋዊ የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ የሰላምና የአንድነት ጉባኤ የሚያደርገውን የድርድር ጥረት እያደነቀ ጥረቱ ግን ሊሳካ የሚችለው ኢትዮጵያ የሚገኙ አባቶችና በስደት ላይ የሚገኘው ሕጋዊ ሲኖዶስ በጋራ ቀርበው ለመወያየት የሚችሉት ትክክለኛና ፍሬ አጀንዳ የሆነው የሕገ ቤተ ክርስቲያን መጣስና የቀኖና መፍረስ እንዴት እንደሚስተካከል ዋነኛ የመወያያ አጀንዳ መሆኑ በሁለቱም ወገን ታምኖበት ሲቀርብ ብቻ መሆኑን አምኖበታል።*

2. *አሁን ባለንበት ዘመን፡-መላው ዓለም በኢኮኖሚ በፖለቲካና በማኅበራዊ ኑሮ የዕድገት እሽቅድምድም በተያያዘበት ጊዜ አገራችን ኢትዮጵያ ግን ከነበረችበት ደረጃ ወርዳ በየጊዜው በሁሉም መልክ እያሽቆለቆለችና ሕዝቧም በረሀብ፤በችግርና ነጻነት በማጣት የመሳሪያ አፈሙዝ ተደቅኖባ በግፍ ታፍኖ፤የመናገር መብቱ ተገፎና ብዙ ወንድሞችና እኅቶችም ያለ አግባብ ከፊሉ በእሥር ቤት፤ከፊሉም በሽሽት እየተሰደዱ ይገኛሉ። የቤተ ክርስቲያን አባቶችም ለእንደዚህ ዓይነት ግፍና መከራ ተባባሪና አስፈጻሚ የመንግሥት አካል በመሆን ፋንታ የቤተ ክርስቲያንን ምክራዊ ድምጽ በመስማት የተረጋጋ ሕብረተሰብ እንዲፈጠር፡ሕዝቡ በልቶ እንዲያድር መንግሥታዊ አስተዳደሩም በዘር፤ በጐሣ፤ በሃይማኖት፤ መከፋፈሉን የሚነቅፍ፤ ሕዝብ ያመነበትና የወከለው የመንግሥት መዋቅር በአገሪቱ ላይ እንዲዘረጋ ስለሚገባ በአገር ውስጥ የሚገኙ የቤተክርስቲያን አባቶችን የወቅቱ ፖለቲካ አራማጅ በሆናቸው ቀርቶ ከሕጋዊ ቅዱስ ሲኖዶስ ጋር በመተባበር ለፍትህና ለ እውነተኛ ዲሞክራሲ እንዲሁም ለሕዝባችን ነጻነት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ጉባኤው ጥሪ አቅርባአል።*

3. *ይህም ሲባል በሰሜናዊው የአፍሪካ ክፍለ አህጉርና መካከለኛው ምሥራቅ አገሮች በቅርቡ እንደተከሰተው፤ የሕዝብና የመንግስት ግጭት አልፎም ደም መፍሰስና ምንም የማያውቀውን ሕዝብ፤ ሕፃናት ወጣቶችና፤ አዛውንቶችን በሰው ሠራሽ መሣሪያ ማጨራረስ ሳይሆን ሕዝቡም በትዕግሥትና በአስተዋይነት ግዴታውን አውቆ በሰላማዊ መንገድ መብቱን ማስከበር እንዳለበት መንግሥትም በራሱ ሕዝብ ላይ እስከዛሬ ያደረሰውን በደል ግፍና ጭፍጨፋ እንዲያቆምና እንደሌሎች መሠል የተበደሉ አገሮች ሕዝብ በሕዝብ እንዲሁም ሕዝብ በመንግሥት ላይ ተነሥቶ እልቂት ከመድረሱ አስቀድሞ እርስ በርስ በመገዳደልና በመጨረራረስ ፋንታ መንግሥት ይህን ተገንዝቦ አስተዳድሩን በአስቸኳይ እንዲያስተካከል ጉባኤው ያስገነዝባል፡፡*

4. *በአሁኑ ወቅት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በውጭና በውስጥ ከየአቅጣጫው የሚሠነዘርባት አደጋ እያየለና በበለጠ እየተጠቃችና ለማዳከምና ብሎም ለማጥፋት*

*የሚደረገው ጥረት ከምን ጊዜውም በከፋ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በቅርቡ በተደጋጋሚ በግብጽና በአገራችንም በኢትዮጵያ በየጊዜው ከምዕመኖቻቸው ጋር የተቃጠሉት አብያተ ክርስቲያናት ለአብነት የሚጠቀሱ ሲሆን፤ እንዲሁም ከውስጥ በቀል የሆኑ ብስለት የጐደላቸውና የአገርና የሃይማኖት ፍቅር ያነሳቸው፤ሳያውቁ ያወቁ የመሰላቸው አንዳንድ በቀል ማኅበሮችና ድርጅቶችም ሕዝብን የሚያሳስትና ሕዝብን በሕዝብ ላይ እንዲነሳ የሚያደርግ ፀረ ኦርቶዶክስ፤ፀረ ቤተ ክርስቲያንና አባቶች የሆነ ወሬ በተለያየ ይብዙኃን ማሰራጫ ዘዴዎችና መሣሪያዎች የሚያስተላልፉትን ሥርዓት አልበኛ ግለሰቦች ጉባኤው እያወገዘ ሕዝቡም ፍሬውን ከገለባ በመለየት እንዲገነዘብና እንዲያስተውል ቅዱስ ሲኖዶስ ያሳስባል፡፡*

*በአጠቃላይ የሚመለከታቸው ሁሉ ይህን የአቋም መግለጫ ለመላው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ቤተ ክርስቲያን ልጆች ሁሉ እንዲደርሳቸው እንዲያደርጉም አሳስቧል፡ በመጨረሻም ጉባኤው አስትናጋጁን የካሊጋሪ ካናዳ ደብረ ምህረት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስና ሕዝበ ክርስቲያኑን ከልብ በማመስገን ሦስት ቀን የፈጀውን ጉባኤ በጸሎትና በቡራኬ ፈጽሟል።*